- ኢየሱስ በተጠመቀበት ወቅት፥እግዚአብሔር አብ ስለ ኢየሱስ ምን አለ?

- እግዚአብሔር አብ ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ መደሰቱን ተናገረ።

- በኋላም መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ዳግመኛ አገኘው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን እንዲህ ሲል ጠራው፡

ዮሐንስ 1፡29

29- ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ «እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤»

- መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን «የእግዚአብሔር በግ» ብሎ ጠራው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን «የእግዚአብሔር በግ» ብሎ የጠራው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ እንዲሞት በግ እንዳዘጋጀ ሁሉ ለሰዎች ሁሉ እንዲሞት እግዚአብሔር ኢየሱስን ስለሰጠ ነው።

- በጉ ሞቶ ደሙ እስራኤላውያንን ከግብፅ እንዳዳነ ሁሉ የኢየሱስ ሞትና ደሙ ሰዎችን ሁሉ እንዲያድን እግዚአብሔር ኢየሱስን ሰጠን።



ትምህርት 48

1. ኢየሱስ ኃጢአት ሠርቶ ያውቃል?

ሀ- አያውቅም።

ሀ- ኢየሱስ ሁሉንም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈጽሟል ኃጢአትም አልሠራም።

2. ኢየሱስ ሁሉንም የእግዚአብሔር ትእዛዝ የፈጸመውና ኃጢአት ያልሠራው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአተኛ ሆኖ ስላልተወለደ ነው።

3. ኢየሱስ ኃጢአተኛ ሆኖ ያልተወለደው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ የሰው አባት የዘር ፍሬ ስላልነበረው ነው።

ለ- ምክንያቱም ኢየሱስ የሰው እናት የዘር ፍሬ ስላልነበረው ነው።

ሐ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

4. እንደ ኢየሱስ ኃጢአት ያልሠራ ሰው አለ?

ሀ- የለም።

ለ- ሌሎች ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነው ተወልደዋል።

5. ዮሴፍና ማርያም በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲያገኙት ኢየሱስ ምን ያደርግ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል መምህራንን እያዳመጠና ጥያቄ እየጠየቃቸው ነበር።

ለ- ኢየሱስ ለእግዚአብሔርን ቃል መምህራን እያስተማራቸውም ነበር።

6. ኢየሱስ ገና የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት አወቀ?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

7. ማርያም በጠየቀችው ጊዜ ኢየሱስ ምን አለ?

ሀ- ኢየሱስ «በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?» አለ።

8. ኢየሱስ እንዲህ ሲል ምን ማለቱ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ እንዲሠራ የፈለገውን ሥራ እየሠራ እንደነበር መግለጹ ነበር።

9. ኢየሱስ በማደግ ላይ በነበረበት ወቅት ለዮሴፍና ለማርያም በትክክል ይታዘዝ ነበር?

ሀ- አዎን።

10. ምንም እንኳን ኢየሱስ እንደ ሌሎች ልጆች ቢሆንም፤ ከሌሎች ልጆች የሚለየው በምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ።

ለ- ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ።

- እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ዮሐንስ የሚባል ልጅ ሰጣቸው።

- የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ልጅ ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ ይባል ነበር።

- እግዚአብሔር መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁድን ሕዝብ ልብ እንዲያዘጋጅ ላከው።

- መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁዶችን ልብ የሚያዘጋጀው ለማን ነበር?

- ለአዳኙ ለኢየሱስ።



- ምክንያቱም ኢየሱስ በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለያስደሰት ስለ ፈለገ ነው።

- ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ነበር።

- ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አብን በሁሉም ነገር ለመታዘዝ ፈለገ።

- ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ይመራው የነበረው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።

- ኢየሱስ በተጠመቀበት ጊዜ ምን ሆነ?

ማቴዎስ 3፡16-17

16- ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው ወጣ፤ ወዲያውኑም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ።

17- እነሆ፣ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።

- እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ተናገረ።

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ልጄ አለው።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው እንዴት ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ሰማይን ለቅቆ የመጣው እግዚአብሔር አብ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ ስለ ነበር ነው።

ማቴዎስ 3፥13-15

13- በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ።

14- ዮሐንስ ግን፣ «ይህማ አይሆንም፤ እኔ ባንተ መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ?» ብሎ ተከላከለ።

15- ኢየሱስም፣ «ግድ የለም ፍቀድልኝ፤ ይህን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና» አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ።

- ኢየሱስ የተጠመቀው ኃጢአቱን ስለተናዘዘ ነው?
- አይደለም።

- ኢየሱስ ኃጢአቱን መናዘዝ ያስፈልገዋል?
- አያስፈልገውም።

- ኢየሱስ ኃጢአቱን መናዘዝ ያላስፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ በፍጹም ኃጢአት አልሠራም።

- ኢየሱስ ለምን ተጠመቀ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እርሱ አዳኝና የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆኑን ለማሳየት ስለ ፈለገ ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ የመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማሳየት ስለ ፈለገ ነው።

- ምክንያቱም ኢየሱስ ለሰዎች ሁሉ መልካም ምሳሌ ለመሆን ስለ ፈለገ ነው።



- መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁዶችን ልብ የሚያዘጋጀው እንዴት ነበር?

- የእግዚአብሔርን ቃል ለእነርሱ በማስተማር።

- እግዚአብሔር መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁድን ሕዝብ እንዲያስተምር መረጠው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ያስተማረው ትምህርት ይህ ነበር፡

ማቴዎስ 3፥1-2

1- በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።

2- ስብከቱም፣ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ» የሚል ነበር።

- መጥምቁ ዮሐንስ አይሁዶችን ምን አስተማራቸው?

- መጥምቁ ዮሐንስ አይሁዶች ንስሓ መግባት እንዳለባቸው አስተማራቸው።

- «ንስሐ መግባት» ምንድን ነው?

- በመጀመሪያ ንስሐ መግባት ስለ እግዚአብሔር ያለንን አስተሳሰብ መለወጥ ነው።

- እግዚአብሔር ስለ እርሱ ያለንን አስተሳሰብ እንድንለውጥ የሚፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እኛ በራሳችን መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደምንችል ስለምናስብ ነው።

- በራሳችን መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን?

- አንችልም።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምንችለው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።

- ንስሐ መግባት ማለት ስለ እግዚአብሔር ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ወደ እርሱ መቅረብ የምንችለው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።

- ሁለተኛው ንስሐ መግባት ስለ ራሳችንን ያለንን አስተሳሰብ መለወጥ ነው።

- እግዚአብሔር ስለ ራሳችን ያለንን አስተሳሰብ እንድንለውጥ የሚፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እኛ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዳልሠራን ስለሚናስብ ነው።

- በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተናል?
- አዎን።

- ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷል።

- ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነው ተወልደዋል።



- መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን በውኃ እያጠመቃቸው ኢየሱስ ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቃቸው ተናገረ።

- መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የኢየሱስን ጫማ ሊሸከም እስከማይገባው ድረስ እንኳን ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ ተናገረ።

- መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሌላ ምን ተናገረ?

ማቴዎስ 3፡12

12- መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ አለ «መንሹ በእጁ ነው፤ ዐውድማውን ያጠራል፣ ስንዴውን በጐተራ ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።»

- መጥምቁ ዮሐንስ ኩራተኞችና ንስሐ መግባት የማይፈልጉ ሁሉ እንደ ገለባ ናቸው አለ።

- ገለባ ለምን ይጠቅማል?

- ለምንም። አይጠቅምም

- ለእሳት ብቻ ነው የሚጠቅመው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ኩራተኞችንና ንስሐ ለመግባት የማይፈልጉ ሰዎችን እንደ ገለባ በዘላለማዊ የእሳት ባሕር ውስጥ ያቃጥላቸዋል አለ።

- አንድ ቀን ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ ሊጠመቅ መጣ።

- አያፈራም።

- ዛፉ ሁልጊዜ መጥፎ ፍሬ ያፈራል።

- መጥፎ ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ ቅርንጫፍ ብንቆርጠው ጥሩ ቅርንጫፍ ሊያወጣና ጥሩ ፍሬ መልሶ ሊያፈራ ይችላል?

- አይችልም።

- ዛፉ ሁልጊዜ መጥፎ ቅርንጫፎችና መጥፎ ፍሬዎችን ነው የሚያፈራው።

- እኛ ሁላችን መጥፎ ፍሬ እንደሚያፈራው ዛፍ ነን።

- እኛ ራሳችንን መልካም ለማድረግ ምንም ነገር መሥራት አንችልም።

- ከኮራንና ንስሐ መግባት ካልፈለግን እግዚአብሔር እንደ መጥፎው ዛፍ ቆርጦ በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ ይጥለናል።

- ከዚያም መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ተናገረ።

ማቴዎስ 3፡11

11- መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ አለ «እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣ ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ ይመጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።»



- ንስሐ መግባት ስለ ራሳችን ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው ምክንያቱም እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለሰራን ነው።

- ሦስተኛ ንስሐ መግባት ስለ ኃጢአት ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው።

- እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት ያለንን አስተሳሰብ እንድንቀይር የሚፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እኛ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እንደሚቀጣ ስለማናስብ ነው።

- እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ሁሉ ይቀጣል?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ሁሉ በዘላለማዊ ሞት ይቀጣል።

- ንስሐ መግባት ስለ ኃጢአት ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በዘላለም ሞት ስለሚቀጣ ነው።

- መጥምቁ ዮሐንስ አይሁዶች ንስሐ መግባት እንዳለባቸው አስተማረ።

- ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረው ይህ ነው፡

ማቴዎስ 3፡3

3- በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረለት እርሱ ነው፤ «በምድረ በዳ፣ ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤ ጎዳናውን አስተካክሉ’ እያለ የሚጮኽ ድምፅ።»

- ነቢዩ ኢሳይያስ መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁዶችን ልብ ለአዳኙ ያዘጋጃል አለ።

- መጥምቁ ዮሐንስ የእግዚአብሔር ነቢይ ቢሆንም እንኳ በጣም ድሃ ነበረ።

ማቴዎስ 3፡4

4- የዮሐንስ ልብስ የግመል ጠጕር ሲሆን፣ ወገቡንም በጠፍር ይታጠቅ ነበር። ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር።

- የመጥምቁ ዮሐንስ ልብሶች ከግመል ፀጉር የተሠሩ ነበሩ።

- አንበጣና የበረሃ ማር ይበላ ነበር።

- አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር ካመኑ እግዚአብሔር ብዙ ገንዘብ እንደሚሰጣቸው ያስባሉ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙ ገንዘብ እንደሚሰጥ ለማንም ቃል አልገባም።

- መጥምቁ ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ያስተምር ስለ ነበር ብዙ አይሁዶች ሊያደምጡት መጡ።

ማቴዎስ 3፡5-6

5- ከኢየሩሳሌም፣ ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐርፉ ነበር።

6- ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር።



- መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የአብርሃም ዘሮች ቢሆኑም እንኳ ይህ እግዚአብሔር እንዲደሰትባቸው ሊያደርገው እንደማይችል ተናገረ።

- ከአንድ ሰው የዘር ሐረግ መወለዳችን እግዚአብሔርን ሊያስደስተው ይችላል?

- አይችልም።

- መጥምቁ ዮሐንስ እግዚአብሔር ከፈለገ ከድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን ማምጣት ይችላል አለ።

- መጥምቁ ዮሐንስ ለፈሪሳውያንና ለሰዱቃውያን ሌላ ምን አላቸው?

ማቴዎስ 3፡10

10- መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ አለ «እነሆ ምሣር የዛፎችን ሥር ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል።»

- መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኩራተኞችና ንስሐ መግባት ስለማይፈልጉት ምን አለ?

- እግዚአብሔር እንደ መጥፎ ዛፍ እንደሚቈጥራቸውና በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጥላቸው ተናገረ።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- መጥፎ ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ ፍሬውን ብንቈርጠው መልሶ መልካም ፍሬ ያፈራል?

- ምክንያቱም የእነርሱ ሥራ እግዚአብሔር በእነርሱ እንዲደሰት እንደሚያደርግ ስላሰቡ ነበር።

- ከምንሠራቸው ሥራዎች እግዚአብሔር ደስ ሊያሰኝ የሚችል አለ?

- የለም።

- እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ብቸኛ ሥራ ምንድን ነው?

- ስለ ኃጢአት ንስሐ መግባት።

- ለሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ብቸኛ ሥራ ንስሐ መግባት ነው።

- ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ እንደሚሰኝ ያሰቡበት ሌላው ምክንያት ምን ነበር?

- ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ከአብርሃም የዘር ሐረግ ስለሆኑ እግዚአብሔር እንደሚደሰትባቸው አሰቡ።

- ከዚያስ መጥምቁ ዮሐንስ ምን አለ?

ማቴዎስ 3፥9

9- መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ አለ 'አብርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን አታታልሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል እላችኋለሁና። »



- ብዙዎቹ አይሁዶች በመጥምቁ ዮሐንስ አማካይነት በተነገራቸው የእግዚአብሔር መልእክት አመኑ።

- እነዚህ አይሁዶች ንስሐ ገቡ እግዚአብሔር እንድያድናቸውም ለመኑት።

- እነዚህ አይሁዶች ንስሐ ስለ ገቡና እግዚአብሔር እንዲያድናቸው ስለ ለመኑ መጥምቁ ዮሐንስ አጠመቃቸው።

- ጥምቀት ምንድን ነው?

- ጥምቀት ሰዎችን በውኃ ውስጥ ማጥለቅና ወዲያውኑ ማውጣት ነው።

- ጥምቀት ምንድን ነው?

- ጥምቀት ንስሐ ስለ መግባታችንና በእግዚአብሔር ብቻ ስለ ማመናችን የሚገልጽ ምልክት ነው።

- ጥምቀት አይሁዶችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ችሏል?

- አልቻለም።

- ጥምቀት አይሁዶችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን ያልቻለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሰዎችን በውኃ ውስጥ ማጥለቅ ሊያድናቸው አይችልም።

- ጥምቀት ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድን ይችላል?

- አይችልም።

- ጥምቀት ከኃጢአታችን ሊያድነን አይችልም።
- ጥምቀት ኃጢአታችንን ሊያጥብና ሊያስወግድልን አይችልም።
- ጥምቀት የኃጢአታችንን ዋጋ ሊከፍል አይችልም።

- አይሁዶችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን የሚችለው ማን ብቻ ነበር?

- አዳኙ ኢየሱስ በቻ ነበር።

- ጥምቀት ንስሐ የመግባታችሁና እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናችሁ እንደሚችል የማመናችሁ ምልክት ነው።

- ብዙዎች ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መጥምቁ ዮሐንስን ለማድመጥ መጥተው ነበር።

- መጥምቁ ዮሐንስ ለፈሪሳውያንና ለሰዱቃውያን ምን አላቸው?

ማቴዎስ 3፡7

7- ብዙ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደሚያጠምቅበት ስፍራ ሲመጡ ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ «እናንት የእፉኝት ልጆች! ለመሆኑ ከሚመጣው ቊጣ እንድታመልጡ ማን መከራችሁ!»

- መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን የእፉኝት ልጆች ብሎ ጠራቸው።



- መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን የእፉኝት ልጆች ብሎ የጠራቸው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በጣም ይኮሩ ስለነበር ነው።
- ምክንያቱም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ንስሐ መግባት ስላልፈለጉ ነበር።

- መጥምቁ ዮሐንስ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን ላይ የሰነዘራቸው ቃላት በጣም ጠንካራ ነበሩ።

- የዚህ ምክንያቱ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በጣም ስለሚኮሩና ንስሐ መግባት ስለማይፈልጉ ነበር።

- እግዚአብሔር ኩራተኞችንና ንስሐ መግባት የማይፈልጉትን ሰዎች አያድናቸውም።

- እግዚአብሔር የሚያድናቸው ኩራተኞች ያልሆኑትንና ንስሐ የሚገቡትን ነው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን ሌላ ምን አላቸው?

ማቴዎስ 3፡8

8- መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ አለ «ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ።»

- ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እግዚአብሔር በእነርሱ እንደሚደሰት አሰቡ።

- ፈርሳውያንና ሰዱቃውያን እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ እንደሚሰኝ ያሰቡት ለምን ነበር?